# <u>አቶ ዮሐንስ ጥሩነህ (ሲይቴ)  እኚህ ነበሩ</u>



**ዮሐንስ ጥሩነህ** 1953 — 2012 **እ.አ.አ**

“ኢትዮጵያ ቆራጥ ልጅዋን አጣች፡፤ እኛም ጓዳችንና ወንድማችንን አጣን። ህመም እየበረታበትና ድካም እየተጫጫነው ከቆመለት ዓላማ ሳያዛንፍና ትግሉን ሳይጠራጠር እስከ መጨረሻ እስትንፋሱ ድረስ ታግሎ ማለፉ በህይወት ላለነው ትልቅ የሞራል ጥንካሬን ይሰጠናል። በትግል ሳይሸነፍ በህመም ተሸነፈ። የወንድማችን ስሙና ታሪኩ በኢትዮጵያ የትግል ማኅደር ለዘላለም ይኖራል። ፅናት ለዘመዶቹና ጓዶቹ”። ከትግል ጓዶቹ




ዮሐንስ (በፓል ቶክ መጠሪያ ስሙ፤ ሲይቴ) እጅግ አስተዋይ አዋቂና ሁለገብ ዕውቀቶችን ከማንበብ ልምዱ ያካበተ የበርካታ ጉዳዮች የዕውቀት ጎተራ ነበር። ከ1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አብዮት እንቅስቃሴ ጀምሮ ገና በለጋ ዕድሜው የተማሪው እንቅስቃሴ አካል በመሆን ሀገሩን ለብልጽግና፣ ሕዝቡን ለመብትና ነፃነቱ ለማብቃት አልሞ በመነሳት የታገለና ያታገለ፣ እስከመጨረሻው እስትንፋሱ እምዬ ኢትዮጵያ፣ ባንዲራዬን እንዳለ ዓለማዊ ሕይወቱን ለሀገርና ሕዝቡ የሰጠ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጅ ነበር።

ሲይቴ እያዝናና፣ እያሳሳቀ፣ እየቀለደ፣ እየኮመከ ስለ ሀገሩና ሕዝቡ ሞጋችና ተሟጋች ለምሆኑ የፓል ቶክ መወያያ መድረክ አባላትና ታዳሚዎች ዛሬ ቤታቸውን ጭር የሚያደርገው አድማቂና አበረታች፣ አስተማሪና ተማሪ፣ አወያይና አታጋይ ወንድማቸውን አጥተዋል። ሲሰደብ፡ ሲዘለፍ፡ በነገር ሲጎሸም፡ በሱ አባባል “ሲቦደስ” “የሚያደርጉትን አያውቁምና ተዋቸው” የሚል፡ ነቀፌታቸውንና ማንጓጠጣቸውን ማስተማሪያ አድርጎ ብዙዎችን የሚገስጽ፣ ሰተታቸውን ማስተማሪያ ያደረገ፣ የሚያኮራ ወገን ነበር። ሲናገር የሚደመጥ፡ መልዕክቱና ቁም ነገሩ ስሜትን እየኮረኮሩ፡ ሳቅና ፈገግታን እየመገቡ የሚደመጡ ናቸው። ሀገሩ ስትነካ፣ ባንዲራው ሲዋረድ፣ ሕዝቡ ሲንቋሸሽ፣ እንዴት ተደርጎ፡ የጎበዝ ያለህ ብሎ ድምጹን ካስተጋባ መመለሻ የሌለው ሙግትና ክርክሩ የበርካታዎችን ጆሮ ያገኘ ለመሆኑ የሚያውቁትና የፓልቶክ ታዳሚዎች ይመሰክሩለታል።

ሲይቴ ለሀገሩና ሕዝቡ ራዕይ ያለው ጠይቆና መርምሮ አውቆ ትግላችን ወዴት መሔድ እንዳለበት ወደኋላ ሳይልና ሳያወላውል አዘውትሮ የሚከራከርና የሚያሳምን ሁላችንንም በእኩል የሚመለከት ጠንካራ ግለሰብ ነበር። በርቱ ይል ነበር አዘውትሮ። ሀገሩ በነፃነት ታጅባ ሕዝቡ የድል አየር ሲተነፍስ እንደማየት የሚያስደስተው አንዳችም ነገር እንደሌለ፣ እንደለፈለፈ፣ እንደወተወተ የተለየን ወገናችን ሁሌም የማንረሳውን ድምጹንና ትዝታውን ለትውልድ ትቶ ያሸለብ የምንኮራበት የሀገር ልጅ ነው።

ኢትዮጵያ አንድ ጠንካራ ተከራካሪዋንና ጠበቃዋን አጣች። ሙግቱንና ጩኸቱን ለሀገርና ሕዝብ እንዳደረገ፡ ያለፈ አኩሪ የዚያ ትውልድ ወገናችን ነው።  ወንድም ሲይቴ በደረሰበት ህመም ቢለየንም የተከበራችሁ ቤተሰቦቹ፡ በመጨረሻው የሕይወት ፈተና ወቅትም አብራችሁ ለነበራችሁ ለተከበራችሁ ጓዶቹና ጓደኞቹ  ዓላማና ፅናቱ ሁሌም ይከተለን።






# የአቶ ዮሐንስ ጥሩነህ አጭር የህይወት ታሪክ

አቶ ዮሐንስ ጥሩነህ ከአባቱ ከአቶ ጥሩነህ አስረሴና ከእናቱ ከወ/ሮ ጥሩ ዓለሙ  በጎንደር ክፍለ ሀገር ልዩ መጠሪያዋ እንኮዬ መስክ በተባለችው ሥፍራ መሀል ጎንደር እ.አ.አ. ጃኑዋሪ 23 ቀን 1953 ዓ.ም. ተወለደ። ዕድሜው ለትምህርት በደረሰ ወቅት  በአቅራብያው በሚገኘው ሰበካ ግምጃ ቤት: ማርያም ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቢጀምርም ብዙ ሳይገፋበት ወደ ዘመናዊው ትምህርት በመቀየር በዚሁ ከተማ በጻድቁ ዮሀንስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ያለውን ትምህርቱን ተከታትሏል። የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቱን በጎንደር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ት/ቤት መከታተል ቢጀምርም ታላቅ ወንድሙ በሥራ ምክንያት ምጽዋ ስለነበር ከሱ ጋር በመሆን የሁለትኛ ደረጃ ትምህርቱን ኤርትራ ምጽዋ ልዑል መኮንን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናቋል። ዮሐንስ በትምህርት ዘመኑ ጠንካራና ጎበዝ ተማሪ የነበረ ሲሆን በዚህም ትጋትና ጥረቱ በወሰደው የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከብዙ ተፈታኞች ብቸኛ ሆኖ በማለፍ አ.አ. ዩንቨርስቲ ለመግባት ዕድል የገጠመው ወገናችን ነበር። በመቀጠልም በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በመግባት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለሦስት ዓመታት በመከታተል ላይ እያለ በወቅቱ በሕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ተሳታፊ በመሆን ትምህርቱን አቋርጦ በሸዋ ክፍለ ሀገር ጫንጮ አውራጃ በአዝማችነት ሄዷል።

የዩንቨርስቲ ትምህርቱን እየተከታተለ ባለበት ወቅት የ1966 የኢትዮጵያ አብዮት ተቀሰቀሰ። በዚህ ግዜ ሁሉንም የኢትዮጵያ ልጆች በእኩልነት የሚያይና ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያስከብር ሕዝባዊ መንግስት አስፈላጊነት ሀገሪቱን በወጠራት ወቅት ዮሐንስ ጥሩነህ የትግሉ ተሳታፊ ነበር። በዚህ ትግል ለሀገሬና ለወገኔ የምከፍለው ድርሻ አለኝ በማለት ገና ከጅምሩ ወደ ትግሉ ጎራ በመቀላቀል በመሪ ድርጅቱ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ወጣት ክንፍ ተመልምሎ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል የህዝብ ልጅ መሆኑን አረጋግጧል።

በወቅቱ የደርግን አፋኝ ሥርዓት ከሚታገሉ ጓዶቹ ጋር በመሆን ዘመቻ በዘመተበት አካባቢ አርሶ አደሮችን በማደራጀትና በመቀስቀስ ለመብታቸውና ለመሬት ባለቤትነታቸው "መሬት ለአራሹ" በሚለው መፈክር ሥር በማታገል ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

ዮሐንስ በወቅቱ በሚያደርገው የዴሞክራሲያ መብትና የሕዝብ መንግሥት ትግል በደርግ አገዛዝ አፈናውና ክትትሉ እየከፋ በመምጣቱ ዘመቻውን በማቋረጥ ወደ ሱዳን በ1967 ዓ.ም. መጨረሻ ሊሰደድ ተገዷል። በስደት በነበረበት ወቅትም ትግሉን በመቀጠል ቢገፋበትም በሀገሩ ምድር ላይ ሆኖ ሊጫወት የሚችለውን ሚና ያህል ሊያረካው ስላልቻለ እራሱን ቀይሮ እንደገና ወደ ሀገር በመመለስ

በጎንደር ክፍለሀገር ደባርቅ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር በመሆን እያስተማረ ከደርግ ሥርዓት ጋር ፍልሚያውን ሳይታክት የተጋፈጠ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጅ ነበር። በመጨረሻም የደርግ አፈናና ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር እየከፋ በመምጣቱ ትግሉን በተጠናከረ መልክ ለመቀጠል በ1969 ዓ.ም ወደ በረሀ ለመሄድ ወሰነ። በጎንደር ተራሮች የትጥቅ ትግል የጀመረውን የኢሕአፓ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ወደ ጎንደር፤ ጠለምት በመጓዝ ተቀላቀለ።

በሠራዊቱ ይሰጥ የነበረውን የሽምቅ ውጊያ ሥልጠና አጠናቆ፡

"…ብረት አነሳሁ
ለትግል ተነሳሁ
ልጓዝ በድል ጐዳና
በተሰዉት ጓዶች ፋና …"

የሚለውን መዝሙር በመዘመር መራራውን ትግል ተያያዘው። አቀበት፡ ቁልቁለት መውረዱን፡ በረሀብና ውኃጥም መሰቃየቱን፡ በበረሃ ንዳድ መንደዱ እና ሌሎችንም ችግሮች ከጓዶቹ ጋር በመሆን ብርታትና ጥንካሬውን እንዲሁም ቆራጥነቱን፡ ለዓላማ ሟችነቱን አረጋግጧል።

የኢሕአፓ ሠራዊት፡ በአንድ በኩል የፋሽስቱ ደርግ፡ በሌላ በኩል በጠባብ ብሔረተኛው ወያኔ ሀርነት ትግራይና ሻቢያ በመታገዝ በተከፈተበት ጦርነት በመጀመሪያ ከትግራይ በመቀጠልም ከጎንደርና አካባቢው መቆየት አልቻለም ነበር። ድርጅቱም አካባቢው ምቹ አለመሆኑን ተረድቶ በወሰነው ውሳኔ መሠረት ዮሐንስ ከጓዶቹ ጋር በመሆን ዳግም ወደ ሱዳን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚወዳትን ሀገሩን ለቆ ሊሰደድ በቅቷል።

ዮሐንስ ጥሩነህ በሱዳን ስደት ሕይወቱ በኢሕአፓ ጥላ ሥር ከሚያደርገው ቀጣይ ትግል ጎን ለጎን በሱዳን የተባበሩት መንግስታት ሕፃናትና የስደተኞች ጉዳይ (UNCHR) በማገልገል በርካታ ስደተኞችንና ጉዳተኞችን ጉዳይ ሲያስፈጽምና ሲረዳ ኖሯል። የሱዳን ፖሊሶች በስደተኛው ላይ ያደርጉ የነበረውን ወከባ ለማስቆምና ለመከላከል ከፍተኛውን ጥረት ያደረገና ስኬታማ ውጤት ያስመዘገበ ወገናችን ነው።

ዮሐንስ በ1973 ዓ.ም. ወደ ሱዳን ከወጣ በኋላ ወደ አሜሪካ በመምጣት በሰሜን አሜሪካ የኢሕአፓ ድርጅታዊ መዋቅርን በማጠናከርና እንቅስቃሴውንም ለማገዝ እንደገና ተቀላቅሎ በተለያዩ ኮሚቴዎች ኃላፊነትን ተቀብሎ አገልግሏል።

ዮሐንስ ጥሩነህ በሰሜን አሜሪካ አትላንታ በኖረበት ወቅት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል እስከ አረፈበት ዕለት ለሀገሩና ለሕዝቡ ነፃነት እንደጮኸ፡ እንደሞገተና እንደተንገበገበ ሕይወቱን የለገሰ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጅ ነበር።

ዮሐንስ በማኅበራዊ ሕይወቱም ሰውን አክባሪ፡ ተግባቢና ተጫዋች ከመሆኑም በላይ በሚኖርበት በአትላንታ ከተማ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ አካሎች ጋር ቀና ግንኙነት ያለውና አቅሙና ችሎታው በፈቀደው መጠን እገዛ የሚያደርግ ወገናችን ነበር።

ዮሐንስ ለሞት የማይደነግጥ፣ በሽታ የማይፈራ፣ ላመነበት ጉዳይ ህይወቱን ለመስጠት የማይመለስ ጎበዝ፣ ጽኑና ደፋር ታጋይና የሕዝብ ልጅ መሆኑን የሚያውቁት ይመሰክሩለታል።

ኢትዮጵያ አንድ ጠንካራ ተከራካሪዋንና ጠበቃዋን አጣች። ጩኸቱንና ጊዜውን ለሀገርና ሕዝብ እንዳደረገ፣ የሞገተ፣ ያስተማረ አኩሪ የዚያ ትውልድ ወገናችን ነው። ወንድም ዮሐንስ በደረሰበት ህመም በህክምና ሲረዳ ቆይቶ ነሐሴ 10 ቀን 2004 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ዮሐንስ ዮናስ የተባለ የአንድ ልጅ አባት ነበር።

በወገናችን ዮሐንስ ከዚህ ዓለም መለየት ለልጁ፣ ለወንድም እህቶቹ ለመላው ቤተሰብ፣ ዘመድ አዝማድና የትግል ጓዶቹ እግዚአብሔር ብርታቱንና ጥናቱን ይስጣችሁ/ይስጠን እንላለን።

የተከበራችሁ ቤተሰቦቹ፣ በመጨረሻው የሕይወት ፈተና ወቅትም አብራችሁ ለነበራችሁ ለተከበራችሁ ጓዶቹና ጓደኞቹ ዓላማና ፅናቱ ሁሌም ይከተለን።

